በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከሴፕቴምበር 1-30/2026 የነበረው የአየር ጠባይግምገማ

# እንዲሁም

# ከኦክቶበር 1-31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2026

አዲስ አበባ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈዉ የሶፕቴምበር ወር በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ ሰሜን ምስራቅ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመጨራሻዎቹ ቀናቶች ላይ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ በሴፕቴምበር ወር በ73 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡

በተጨማሪም በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50-76.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል አቦሞሪንጋ 62.4፣ አይራ 76.6፣ አታንጎ 60፣ ጨለንቆ 76፣ ዳሊፉጊ 63፣ ደብረማርቆስ 68.8፣ ማንኩሽ 60፣ ማሻ 60፣ መተማ 72.8 ይገኙበታል ፡፡




ምስል1: ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቦርና፣ ምስራቅ ቦርና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ደቡብ ወሎ፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኙዋክ፣ ኑዌር እና መዥንግ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል ቆራሄ፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ ላይ ከ81-350 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ8-30 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቦርና፣ ምስራቅ ቦርና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የአዊ፣ ምዕራብ ጎጃም እና ባህርዳር ዙሪያ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኙዋክ፣ ኑዌር እና መዥንግ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች ከሶማሌ ክልል ቆራሄ፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ በአብዛኛ መደበኛ እና ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከመሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው ፍሬ በመሙላትና በማበብ ላይ ባሉ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም ቀስ በቀስ በተለይም በሦስተኛው አስር ቀናት ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋዉ እርጥበት በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ከመኖሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳልፈነው ወር በሁሉም የአገራችን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የገፀ-ምድር ውሃ ፍሰት የተመዘገበ ሲሆን፣ ይህም ለአገሪቱ አጠቃላይ የውሃ ሀብት ክምችት፣ ለተፋሰሶች ውሃ መጎልበትና ለውሃ አቅርቦቱ እጅግ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ከፍተኛ የሆነ የገፀ-ምድር ውሃ ፍሰት የነበራቸው ሲሆን፣ በአፋር ደናክል እና በኦጋዴን አካባቢዎች ደግሞ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የገፀ-ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ እነዚህ የተገኙት የገፀ-ምድር ውሃ ፍሰቶች በየተፋሰሶቹ ለሚገኙ ዋና ዋና ግድቦችንና ለውሃ አካላት አዎንታዊ አስተዋጽዖ ነበረው(ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2026
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2. መግቢያ

የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያጠቃልል ሲሆን፤ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ በመሆኑም የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ ለደቡብ አጋማሽ አከባቢዎች የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው። በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት የክረምት የዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ

## 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የበጋ ወቅት እንደሚስተዋለው የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ከመታየቱ አንጻር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመር ያሳያል፡፡

በመጪዉ የኦክቶበር ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሁኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ያገኛሉ (ካርታ 13)፡፡ በመሆኑም በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዩጵያ ዞኖች፣ የሶማሌ ደቡባብዊ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 14) ። በተጨማሪም በጸሀይ ሀይል በመታገዝ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት የምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር ወር በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ያለውና የተሻለ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፤ በተጨማሪም በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የሚያስፈልጋቸውን የውሃ አቅርቦት መሟላት የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በሂደትም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄደው እርጥበት ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሰብል አምራች በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በስፋት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ነው።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የኦክቶበር ወር በሀገራችን ተፋሰሶች ላይ የሚኖረው የገፀ-ምድር የውሃ ፍሰት በባሮ አኮቦ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ ሠበላይኛው የዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ-ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። ይህም የውሃ መጠን መጨመር በእጅጉ የሚያጎለብት ይሆናል። ይህ አዎንታዊ ሁኔታ በዋናነት የበጋ ወቅት የውሃ ተጠቃሚ ለሆኑት የሀገራችን ተፋሰሶች፣ እና የልማት ዘርፎች የተሻለ የሆነ የገፀ-ምድር የውኃ ሀብት የሚገኝበት የተሻለ ወር ይሆናል። ይህም ለእንስሳት መጠጥ፣ ለኃይል ማመንጫዎች እና ለተለያዩ አጠቃላይ የውሃ ፍጆታዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በተጨማሪም በአብዛኛው የአፋር ደናክል በመካከለኛው እና በታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ እንዲሁም ስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ላይ መካከለኛ መጠን ያለው የገፀ-ምድር የውሃ ፍሰት የሚመዘገብ ይሆናል።

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et